የጾመ ነቢያት (የገና ጾም) ስያሜዎች በቤተ ክርስቲያን

ለተወሰነ ጊዜ እህል ከመብላትና ውሃ ከመጠጣት መታቀብ ወይም ለተወሰኑ ወራት ከጥሉላት፥ ከሥጋ፥ ከቅቤ፥ ከወተት፥ ከእንቁላል፥ በዘጠቃላይ ከእንስሳት ውጤት መከልከል ነው። ይህ ብቻ ጾምን ፍጹም ስለማያደርግ ቅዱስ ያሬድ ሕዋሳት ሁሉ በየራሳቸው ክፉ ከመሥራት መጠበቅ አለባቸው ብሎአል። ይኸውም ዓይን ክፉ ከማየት፥ ጆሮ ክፉ ከመስማት፥ ምላስ ክፉ ከመናገር ይከልከሉ። በተጨማሪም አእምሮን ጐድተው ሰውን አስከረው የማይገባ ከሚያሠሩና ከሚያሳስቡ የአልኮል መጠጦችም መጠበቅ እንዳለብን ማወቅ ይገባናል።

ጾም የሥጋን ምኞት የምታጠፋ (የኃጢአት ምኞት ማለት ነው) የነፍስን ቁስል የምታደርቅ ለጎልማሶችም ጸጥታንና ርጋታን የምታስተምር፥ ከእንስሳዊ ግብርና ጠባይ የምትከለክልና ሰው መላእክትን መስሎ የሚኖርባት ደገኛ ሥርዓት ነች።

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለጾም ሥርዓትና ደንብ አውጥታለች። በዓመት ውስጥ ሰባት የአዋጅ አጽዋማት እንዳሉና ማንኛውም ክርስቲያን እነኚህን አጽዋማት እንዲጾም ታዛለች። ከነዚህ አባቱ አጽዋማት መካከል አንዱ ጾመ ነቢያት ነው።

ይህ ጾም ከኅዳር ፲፭ ጀምሮ ለ፵፫ ቀናት የሚጾም ሲሆን ፋሲካው በልደት በዓል ነው። ይህን ጾም በዘመነ ብሉይና በዘመነ ሐዲስ ብዙ ቅዱሳን ጾመውታል። በቤተ ክርስቲያናችንም የሚከተሉት ሥያሜዎች አሉት።

ሀ. <u>ጾመ አዳም ይለዋል፦</u>

ለአዳም የተነገረው ትንቢት ስለ ተፈጸመበት። አዳም ዕፀ። በለስን በልቶ ከገነት ከተባረረ በኋላ በፍጥረቱ ገሸር አድርጎ በገነት ያኖረኝን ፈጣሪዬን ትቼ የፍጡርን ቃል ሰምቼ ትእዛዙን አፍርሼ አሳዘንኩት ብሎ በፈጸመው በደል አዝኖ ተክዞ አለቀሰ፥ ጾመ፥ ጸለየ። ከልብ የሆነ ጸጸቱንና ዕንቡን በራሱ መፍረዱንም አይቶ እግዚአብሔር ተስፋ ድኅነት ሰጠው። «በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለእለት እትወለድ እም ወለተ ወለትከ ወእድህከ ውስተ መርኅብከ፤ ወእትቤዘወከ በዕፀ መስቀልየ ወበሞትየ ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ በደጅህ ድኼ በዕፀ መስቀል ተሰቅዬ ሙቼ አድንሃለሁ» የሚል። አዳምም «በሐሙስ ዕለት» ያለውን እንደ እርሱ አቆጣጠር መስሎት እስከ አምስት ቀን ጠበቀ። በኋላ ግን አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም በፈቃዴ ተገርፌ ተገፍፌ በዕለተ ዓርብ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅዬ ሥጋዬን ቆርሼ ደሜን አፍስሼ ሞቼ ተነሥቼ አድንሃለሁ እንዳለው ተረድቶ ይህን ተስፋ በመትከፈ ልቡናው ተሸከሞት ይኖር ነበር። ነጋዴ ስንቁን ይዞ እየበላበት ከዚህ እስከዚያ ያደርሰኛል እያለ እንዲጓዝ በአፀደ ሥጋም በአፀደ ነፍስም ሳለ ጌታዬ እንዲህ ብሎኛልና ይምረኛል እያለ ተስፋውን አጽንቶ ሲጠባበቅ ኖረ። ለልጆቹም ሁሉ ነገረ። ትንቢት ተነገረ ሱባዔ ተቆጠረ። ፭ ሺህ ፭፻ ዘመን ሲፈጸምም የማያደርገውን የማይናገር የተናገረውንም የማያስቀር ጌታ «ቀን ቢደርስ አምባ ይፈርስ» እንዲሉ ከዘመኑ ዘመን፥ ከወሩ ወር፥ ከዕለታቱ ዕለት፥ ከሰዓቱ ሰዓት ሳያጓድል በጽኑዕ ቀጠሮው የአዳም የልጅ ልጅ ከምትሆን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ። ገላ ፪፥፩። ስለዚህ ጾሙ የተሰጠው ተስፋ የተቆጠረው ሱባዔ ስለተፈጸመበት «ጾመ አዳም» ይባላል።

ለ. <u>ጾመ ነቢያት ይለዋል፦</u>

ነቢያት የተናገሩት ትንቢት ስለ ተፈጸመበት። በየዘመናቱ የተነሡ ነቢያት እግዚአብሔር ወደ ፊት ሊያደርግ ያሰበውን በእምነት ዓይን እያዩ ምሥጢር ተገልጦላቸው የራቀው ቀርቦ የረቀቀው ገዝፎ እየተመለከቱ ትንቢት ተናገሩ፤ ያዩትም መልካም ነገር እንዲደርስላቸው ጾሙ ጸለዩ። ነቢያት ስለመወለዱ፥ ወደ ግብፅ ስለ መሰደዱ፥ በባሕረ ዮርዳኖስ ስለ መጠመቁ፥ ብርሃን በሆነው ትምህርተ ወንጌል ጨለማውን ዓለም ስለ ማብራቱ፥ ለሰው ልጆች ድኅነት ጸዋተወ መከራ ስለ መቀበሉና ስለ መሰቀሉ፥ ስለ ትንሣኤው፥ ስለ ዕርገቱና፥ ስለ ዳግም ምጽአቱ ትንቢት ተናግረው አላቆሙም፤ ለአዳም የተሰጠው ተስፋ ተገልጦላቸው ለተናገሩት ትንቢት ፍፃሜ እንዲያደርሳቸው ፈጣሪያቸውን ተማፀኑትም እንጂ። በየዘመናቸው «አንሥእ ኃይለከ፣ ፈኑ እዴከ» እያሉ ጮኹ። በጾምና በጸሎት ተወስነውም ሰው የሚሆንበትን ጊዜ በቀናት፣ በሳምንታት፣ በወራትና በዓመታት ቆጠሩ። ለምሳሌ ነቢዩ ኤርምያስ ስለ ሥጋዌው ትንቢት በተናገረ በ፭፻፸፭ ዓመት ጌታችን ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው ሆኗል።

ነቢያት ተስፋው በዘመናቸው ተፈጽሞ በዓይነ ሥጋ ለማየት ባይችሉም እግዚአብሔር «አያደርገውን አይናገር የተናገረውን አያስቀር» ብለው አምነው ከወዲሁ ተደሰቱ። ለዘመነ ሥጋዌ ቅርብ የነበሩት እለ ኢሳይያስ ጾሙ እንዴት መፈጸም እንዳለበት ተናግረዋልም። ኢሳ ፶፰፥፭። በመሆኑም በጌታ ልደት ትንቢተ ነቢያት ስለ ተፈጸመበት ይህ ጾም «የነቢያት ጾም» ይባላል። የወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን ያስተማሩበት ስለሆነም «ጾመ ስብከት» ይባላል።

ሐ. ጾመ ሐዋርያት ይለዋል፦

ሐዋርያት «ትንሣኤን ዓቢይ ጾምን ጾምን እናከብራለን፣ ልደትን ምን ሥራ ሠርተን እናከብራለን» ብለው ከልደተ ክርስቶስ በፊት ያሉትን ፴፫ ዕለታት ጾመዋልና። የጾሙ መጨረሻ (መፍቻ) በዓለ ልደት ስለሆነም «ጾመ ልደት ይባላል።

መ. ጾመ ፊልጶስም ይለዋል

ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ ወደ አፍራቂያና አውራጃዋ ሁሉ ወጥቶ በጌታችንና አምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አስተማረ። ልቡናን የሚያስደነግጥ ድንቅ ድንቅ ተአምራትንም አደረገ፣ ብዙዎችንም እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ መለሰ። ወደ ሌሎች ብዙ አገሮችም ተዘዋውሮ የከበረ የወንጌልን ቃል በማስተማር ሰዎችን ወደ ሃይማኖት ሲጠራ ኖረ። ብዙዎችንም ክብር ይግባውና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አሳመነ። ያላመኑት ግን ከንጉሡ ዘንድ ተመካክረው ይዘው አሠሩት። ጽኑዕ ሥቃይንም አሠቃዩት። እርሱ ግን ከዘለዓለም ሕይወት ስለ ምን ትርቃላችሁ? የነፍሳችሁንስ ድኅነት ለምን አታስቡም? ይላቸው ነበር። እነርሱም ልቡናቸው ደንድኗልና ብዙ መከራ ካጸኑበትና ካሠቃዩት በኋላ ኅዳር ፲፯ ቀን ዘቅዝቀው ሰቀሉት፤ ነፍሱንም በእግዚአብሔር እጅ ሰጠ። ሥጋውን በእሳት ሊያቃጥሉት በወደዱ ጊዜ ከእግዚአብሔር የተለካ መልአክ ከእጆቻቸው መካከል ነጠቃቸው እያዩትም ወስዶ ሠወረው። ይህንንም ተመልክተው ስለገደሉት ተጸጽተው ያዘኑና ያመኑ ብዙዎች ቢጾሙና ቢጸልዩ ቢለምኑ ሰውን የሚወድ ቸው ይቅር ባይ ጌታችን ልመናቸውን ተቀብሎ በ፫ ቀን መልሶላቸው በፍጹም ደስታ አሳረፋት። ይህን ያዩ ሁሉ ወደ እምነቱ ገቡ። ከሐዋርያ ፊልጶስም ሥጋ ታላላቅ የሆኑ ድንቅ ድንቅ ተአምራት ተገልጠዋል። ደቀ መዛሙርቱ ግን ጾሙን ጀምረን አንተወውም ብለው እስከ ልደት በዓል ድረስ ጾመውታል። ስለዚህ ነገርም ጾሙ «ጾመ ፊልጶስ» ይባላል።

ሠ. ጾመ ማርያምም ይለዋል፦

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጾማዋለችና። ይህም ቅዱስ ገብርኤል ወልደ አምላክን ያለ ሰስሎተ ድንግልና በግብረ መንፈስ ቅዱስ ፀንሳ እንደምትወልደው ካበሠራት በኋላ እመቤታችን ትሑት ናትና ሰማይና ምድር የማይወስኑትን አምላክ ፀንሼ ምን ሰርቼ እወልደዋለሁ ብላ ጌታን ከመውለዷ አስቀድማ ጾማዋለችና «ጾመ ማርያም» ይባላል።

ይህን ጾም ነቢያትና ሐዋርያት ጾመውት በረከት አግኝተውበታል፤ በመሆኑም የቤተ ክርስቲያን አባቶች ምእመናን በመጾም እንዲጠቀሙበት ሥርዓት ሠርተዋል። ይህን ሥርዓት በመያዝ ባለፉት ዘመናት የነበሩ ምእመናን ጾመውት በረከት አግኝተውበታል። ዛሬም እንጾመዋለን። ክብር ይግባውና ጌታችን ለፍርድ መጥቶ ለእያንዳንዱ እንደየሥራው በሚያስረክብበት ጊዜ በቀኙ እንዲያቆመንና የአባቴ ቡሩካን ኑ ብሎ መንግስቱን ከሚያወርሳቸው ቅዱሳን ጋር እንዲደምረን አምላክ ነቢያት ወሐዋርያት፥ አምላክ ጻድቃን ወሰማዕታት ተለመነን እያለን እንማጸንበታለን።

እግዚአብሔር አምላካችን ጾሙን የበረከት ያድርግልን አሜን።

ምንጭ ፦

ዓምደ ሃይማኖት (በመምህር ብርሃኑ ጎበና)

ጾምና ምጽዋት (በዲ ቃኘው ወልዴ)